ጉባዔ አምስት::

አንቲ ውእቱ ተስፋሁ ለአዳም አመ ይሰደድ እምገነት::

አበው ቀደምት ያለውን ይተረትራል አመ ተሰደ ሲል ነው መጽሐፍ ነላፍያትን መጻእያት፤ መጻእያትን ነላፍያት አድርጎ መናገር ለመጽሐፍ ልማድ ነው፤ አመ ይወጽኡ እስራኤል እምግብጽ፤ ወአመ ይትበሃሉ ለሰይጣን፤ ወአመ ይመጽእ ወልደ እጓለ እመሕያው በስብሐቲሁ እንዲል፤ አዳም ከገነት በተሰደደ ጊዜ በመትከፉ ልቡናው ቋጥሮ ይዞሽ የወጣ አለኝታ ስንቁ ተስፋው ጸሎቱ አንቺ ነሽ:: ይህስ እንደምንድን ነው ቢሉ ጌታ አዳምንና ሔዋንን ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ ከአምስተኛ ባሕርየ ነፍስ ፈጥሮ በነፍስ ሕያዋን አድርጎ በልጅነት አክብሮ በጸጋ አስጊጦ በገነት አኖራቸው ሰባት ዓመት በሕጉ ጸንተው ሕጉን አክብረው አትብሉ ያላቸውን ዕፀ በለስ ጠብቀው ኖሩ፤ ኋላ ግን አትብሉ ያላቸውን ዕፀ በለስ በልተው ቢያሳዝኑት በሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ በርደተ መቃብር ርደተ ሲኦል ፈረደባቸው፤ ከገነት አውጥቶ በገነት አንፃር በደብር ቅዱስ አኖራቸው:: ስለምን ቢሉ የገነት ጣዕሟን መዓዛዋን እያሰቡ በጎዘን ላይ ጎዘን በመከራ ላይ መከራ እየጨመሩ እንዲፀፀቱ ብሎ:: አንድም ተስፋ እንዳይቆርጡ ከዚህ ያኖረን ሊመልሰን ይሆናል እንጂ እያሉ:: ከዕለታት አንድ ቀን አዳም ሔዋንን በክፉ ዐይን አያት ሴቶች ድንጉጦች ናቸውና ጥላ ጠፋች፤ መልአኩ መጥቶ ሔዋንን ለምን ሰደድሃት? አለው:: ምን ላድርግ በሷ ምክንያት እግዚአብሔርን ያህል ጌታ ገነትን ያህል ቦታ ሳጣ አለው፤ ኋላ የምታስታርቅህ እሷ ናትና ከሷ አትለይ፤ አሁን ሄደህ አምጣት አለው:: ኢትከውነኒ ዐራቂተ እሷስ ከማጣላት በቀር አታስታርቀኝም አለው ከዚህ በኋላ መላእክት ጸሎት ማድረስ ሱባኤ መያዝ አስተምረውት ነበርና ሲጸልይ መልአኩ መጥቶ አዳም! ቂም በቀል ይዘህ ብትጸልይ

---

51 ማርያም ሆይ ርኅራኄሽ የሕፃንን መቅሰፍት ያስጣለው የልጅሽን ትእዛዝ በማጉደል በአንቺ የተማፀነውን መልአክ ከባልንጀራው (ከአጎራባቹ) ጋር ለመቆም በተሳነው ጊዜ በቀልሞን ተራራ ሳሙኤል በጸለየ ጊዜ የሥዕልሽ ተአምር ወደ ሰማይ አወጣው:: ማኅሌተ ጽጌ

ምን ይረባሃል የቁመኛን ጸሎት እግዚአብሔር አይቀበለውም፤ ጸሎቱ
ለመስተቀይም ከመ ዘርእ ዘወድቀ ማዕከለ አሥዋክ እስመ ዘያነብር
ቁመ ወበቀለ ኢውክፍት ጸሎቱ ቅድመ እግዚአብሔር እንዲል። ይልቅስ
ታረቃት አለው አንተ ሄደህ አምጣልኝ አለው አንተው እንዳባረርካት
ራስህ ሄደህ አምጣት ብሎት አዳም ሄዶ አምጥቷታል፤ እሷም መጥታ
ከጫማው ወድቃ ማረኝ ብላለች። ይህ ዛሬ ድረስ ለሴቶች ልማድ
ሆኖላቸው ሴት ምንም ድህ ብትሆንና ብትበድልም ወንድ ሄዶ
ይማልዳታል እንጂ ሴት ሄዳ አትማልደውም። ከዕለታት አንድ ቀን
ሔዋን አዳምን፤ አዳም! አለችው፤ አቤት አላት፤ አሁን ቀኖና ብንገባ
ፈጣሪያችን ይቅር አይለንም? አለችው። እንዴት ይቅር አይለን ነገር
ግን አንቺ አለሽና ታድያ ምን ይሆናል አላት፤ እንግዲህ ወዲህስ
ከፈቃድህ አልወጣም አለችው፤ ከሆነማ ይሁና ብሎ እንደ መቀስ
ከምትቆራርጥ እንደ ሰይፍ ከምትከፋፍል ቀዝቃዛ ባሕር ውስጥ እሷን
ጥቂት እልፍ አድርጎ ቀኖና ገቡ። ስለምን ቢሉ ፆር እንዳይነሣበት፤
አንድም መልአኩ አትለያት ብሎ ነበርና። አንድም ምቅዋሞን
ወምጽላዮን ለአንስት ለባሕቲቶን የምትል ሕገ ኦሪት እንደምትሠራ
በልቡናው ተገልጦለት። ሠላሳ ዘጠኝ ቀን ሲሆናቸው ሰይጣን መጥቶ
አዳም! ፈጣሪህ ይቅር ብየሃለሁና ውጣ ብሎሃል አለው፤ አንተ ማነህ?
አለው። እኔ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ነኝ አለው። አዳምም ቀድሞ
የፍጡር ቃል ሰምቼ ከዚህ ሁሉ መከራ ደረስኩ እንግዲህስ ወዲህ ራሱ
መጥቶ ይቅር እንዳለኝ ካልነገረኝ በስተቀር አልወጣም አለው። ከዚህ
ቀድሞ አትብላ ያለህን ዕፀ በለስ በልተህ ይህ ሁሉ መከራ ደረሰብህ
ደግሞ ዛሬ ፈጣሪህ ይቅር ብየሃለሁና ውጣ ብሎሃል ብዬ ብነግርህ
አልወጣም አልክ? እኔማ ምን ቸገረኝ፤ ለላከኝ እነግርልሃለሁ እንጂ
ብሎ የተቆጣ መሰሎ፤ ለመሆኑ ሔዋን የት ነው ያለችው? አለው።
ከዚያ አለችልህ አለው ወሐረ ኀበ ገራኅተ ሐምሉ ይላል የኅመን
መዝሪያው ጓሮው ናትና፤ ወደ ሔዋን ዘንድ ብሄድ ሔዋን ሥራ ፈት
ሆና አገኛት፤ ሔዋን! በዚህ በባልሽ በአዳም እወቂበት ቀድሞ ፈጣሪው
አትብላ ያለውን ዕፀ በለስ በልቶ ከዚህ ሁሉ መከራ ደረሰ ዛሬ ደግሞ
ፈጣሪህ ይቅርብሎሃልና ውጣ ብዬ ብነግረው አልወጣም አለ አላት።
አንተ ማነህ? አለችው፤ እኔ መልአከ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ነኝ
አላት። ውይ ሌላ መስለኸው ይሆናል እንጂ ብላ መሰስ ብላ ወጥታ

Scanned by CamScanner

ሄኖ፤ አዳም፣ ፈጣሪያችን መሓሪ ወመስተሣህል ነው ስንኳን በዚህን ያህል ቀን ቀርቶ በአንድ ቀንስ ይቅር ቢለን ይቻለው የለምን? ፈጣሪያችን ይቅር ብሎናልና ውጣ አለችው። ይወዳታልና መልአኩም አትለያት ብሎት ነበርና እኔ ሌላ መስሎኝ ነው እንጂ ብሎ ተከትሏት ወጣ። ይህም ዛሬ ዲያብሎስ ሔዋንን ሔዋን አዳምን ድል መንሣት ልማድ ነው። እሱ በፊት በፊት እነሱ በኋላ በኋላ ሆነው ሲሄዱ ከእግረ ደብር ሲደርሱ እኔ ማነኝ አላወቃችሁኝም? አላቸው። ኧረ እኛስ አላወቅንህም፤ ምነው ቅድም መልአከ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ነኝ አላልኸንም? አሉት። ምን መልአከ ብርሃን መልአከ ጽልመት እንጂ ቀድሞ ከገነት ያወጣኋችሁ ጥንተ ጠላታችሁ እኔ ጋርዳኤል ነኝ ብሎ፤ ዘወር ብሎ ቢያያቸው ጨለማ ዋጣቸው። ደንግጠው ወደቁ፤ ሦስት ቀን ለነበቱ በሦስተኛ ቀን መልአኩ አንሥቶ በደብር ቅዱስ አኖራቸው ከዚህስ ማኖሩን አናርከን። የምግባችን ነገር እንደምን ይሁን? አሉት። ቆዩ ለላከኝ እነግርላችኋለሁ ብሎ ሄዶ በገነት ላሉ አዕዋፍ ጌታችሁ አዳም ከፈጣሪው የሚታረቅበት ጊዜ ደርሷል ኋላ ልጆቹ ልጆቻችሁን እንዳይከለክሏቸው ምግቡን ወስዳችሁ ስጡት አላቸው። እነሱም አንድ አንድ ዘለላ ፍሬ ወስደው ዐሥራ ሁለት ዋሻ መልተውታል። እያንዳንዱ ዋሻ ሠላሳ ሠላሳ ምንዳፈ ሐፅ የሚያስወረውር ነው። ምንዳፈ ሐፅ ማለት አንድ ብርቱ አርበኛ ጦር ወርውሮ የሚያሳርፍበትን ያህል ማለት ነው። ከዕለታት አንድ ቀን አዳም አዕዋፍ የሚሄዱበትን ቀን አወቀ በምን ቢሉ ቋንቋቸው አንድ ዕብራይስጥ ነበርና። አንድም በመንፈስ ቅዱስ ተገልጦለት የአራዊትን የአእዋፋትን የእንስሳትን ቋንቋ ያውቅ ነበርና፤ ዘአራዊት ንቃወ ወዘአዕዋፍ ድምፀ በመንፈስ ያዕቆብ አእመረ ወለበወ እንዲል። የአዳም ወዳጆች አብሪል አዝሪል የሚባሉ መልከ መልካሞች ድምፀ መልካሞች አዕዋፍ አሉ። አዳም ኃያል ነውና እሱ በእግር ሆኖ እነሱ በክንፍ ተካክለው ከእግረ ገነት ደረሱ። የገነት ቅጽሯ እሳት ነው፤ እነሱ ላይ ላዩን እየበረሩ ከገነት ገቡ እሱ መግቢያ አጥቶ ቆሞ ሳለ ሰይጣን አይቶት ይህን ጁጁ ሽማግሌ ደግሞ ዛሬ ከዚህ ምን አመጣው እንዲያውም ካልገደልኩት አላርፍም ብሎ ደንጊያ አንሥቶ መሐል አገዳውን ሰበረው ደሙ በደንጊያ ተቋተ፤ ወተደብተረት ይእቲ ዕብን ላዕለ ርእሰ አዳም ሠሉሰ መዋዕለ ወሠሉሰ ለያልየ ይላል ሦስት ቀን

እንደ ድንኳን ሆናለት ሦስት ቀን አድሯል በሦስተኛው ቀን መልአኩ መጥቶ አንሥቶለታል። ይህ ምሳሌ ነው፤ ከዚያ ሦስት ከዚህ ሦስት ቀን ስነበቱ ስድስት ይሆናል የሰሙነ ሕማማት ምሳሌ፤ አንድም የስድስቱ ቃላተ ወንጌል ምሳሌ፤ አዳም የጌታ ዕብን የመቃብር፤ ደመ. ፈሶ ነበርና ደሜ ፈሶእንዲሁ ይቀራልን ብሎ ከፍሬ በለስ ጫምሮ መሥዋዕት አቀረበ ያሁኑን መሥዋዕትህን ተቀብዬልሃለሁ እንግዲህ ወዲህ አትሠዋ ዓለም የሚድነው በዕሩቅ በእሲ ሥጋና ደም አይደለም፤ አካላዊ ቃል በተዋሐደው ሥጋና ደም ነው እንጂ፤ ብሎ በጎመ.ስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ ወእድሕክ ውስተ መርሕብከ ወእትቤዘወከ በመስቀልየ ወበሞትየ በአምስት ቀን ተከል ከልጅ ልጅህ ተወልጄ ሞቼ ተሰቅዬ አድንሃለሁ ብሎ ተስፋውን ነገሮታል። ከዚያን ሰዓት ጀምሮ እመቤታችንን ተስፋ ያደርግ ነበርና አዳም በመትከፈ ልቡናው ይዞሽ የወጣ አለኝታ ስንቁ ተስፋው ጸሎቱ አንቺ ነሽ አለ። አዳም ማለት ይህ ቀረህ የማይባል ፍጹም ፍጥረት እጥር ምጥን ያለ መልከ መልካም ማለት ነው፤ አንድም ዘተሠገወ እመሬት ማለት ነው።።

የውኃቱ ለአቤል ዘተቀትለ በዐመፃ።።

እመቤታችንን በበጎ ይመስላታል አቤል የውኃነትን መያዙ በእመቤታችን ምክንያት የሚገኘውን ክብር አገኛለሁ ብሎ ተስፋ አድርጎ ነውና ይህስ እንደምንድን ነው ቢሉ ሳይገድል የተገደለ ሳይበድል የተበደለ የአቤልን የየዋህነቱን ዋጋ የምታሰጭው አንቺ ነሽ። አዳም በዐሥራ አምስት ቀን ሩካቤ ሠላሳ፤ በሠላሳ ቀን ሩካቤ ስልሳ መንታ መንታ ልጅ ወልዷል። ወደ ፊት ባዕድ ከባዕድ እንጂ ዘመድ ከዘመድ አትጋቡ የምትል ሕገ አሪት እንደምትሠራ በልቡናው ተገልጦለት፤ ዕለተ ፅንስ ካገናኛቸው ይልቅ ዕለተ ፅንስ ያላገናኛቸው ይርቃሉ ብሎ ያራራቀ መስሎት፤ ለእኅተ አቤል ያውስባ ቃኤል ወለእኅተ ቃኤል ያውስባ አቤል፤ የአቤል መንትያን ቃየል ያግባ፤ የቃየል መንትያን አቤል ያግባ ብሎ አዘዘ። የቃኤል መንትያ ሉድ ትባላለች ወትመስል ሔዋንሃ እማ ይላል መልከ መልካም ናት። የአቤል መንትያ አቅሌማ ትባላለች፤ መልከ ጥፉ ናት።። ቃኤል ይህን ሰምቶ የኔን መልከ መልካም ለሌላ የሌላ ክፉ መልከ ጥፉ ለኔ ምን ቢያገደው አይሆንም አለ። አዳምም ይህንን ሰምቶ እኔ አዝገሮችኋለሁ። አይሆንም ካላችሁ

መሥዋዕት ሰውታችሁ መሥዋዕቱን የተቀበለለት ያግባት አለ።
ለጊዜው ፈቃደ እግዚአብሔር ለሁሉ እንደ ሆነ ሲያጠይቅ ነው።
ፍጻሜው ግን መሥዋዕት ለማስተማር ነው። አቤልን ወክነ አቤል
ኖላዊ አባግዕ ይለዋል በግ ያረባ ነበር፤ እግዚአብሔር እንጂ ንጹሐ
በሕርይ ነው ንጹሕ ነገር ይወዳል ብሎ ከሚጠብቃቸው በጎች ቀንዱ
ያልከረከረውን ጸጉሩ ያላረረውን ጥፍሩ ያልዘረዘረውን ዓመት የሆነውን
ጠቦት አርዶ አወራርዶ አቀረበ። አሁን አቤልን እግዚአብሔር ንጹሐ
በሕርይ ነው ንጹሕ ነገር ይወዳል ማለትን አባቱ ነግሮት መምህር
አስተምሮት ከመጻሕፍት አግኝቶት አይደለም። አበቦች በባሕርያቸው
እንዲያብቡ ንቦች በባሕርያቸው እንዲራቡ አቤልም በአዕምሮ ጠባይዕ
አውቆ ከራሱ አንቅቶ ነው እንጂ። አቤልሰ አስረፀ ጽድቀ እምነፍሱ
እንዲል። ወነጸረ እግዚአብሔር ላዕለ አቤል ወላዕለ መሥዋዕቱ
ይላል[52]፤ እግዚአብሔርም የልቡን ቅንነት የመሥዋዕቱን ደግነት አይቶ
መሥዋዕቱን በብሩህ ገጽ ተቀብሎለታል፤ በምን ታውቋል ቢሉ እሳት
ከሰማይ ወርዶ በልቶለታል። ቃኤልን ወክነ ቃኤል መስተገብረ ምድር
ይለዋል፤ የተዘራውን የሚሰበስብ የበቀለውን የሚያጭድ ገበሬ ነው።
መቼስ እግዚአብሔር ለእኛ ብሎ ነው እንጂ እሱ አይበላውም ቢቀበለው
ይቀበለው ባይቀበለው የራሴን እጎት ማን ነሥቶኝ ብሎ ውርጭ
የመታውን ዋግ የበላውን ስንዴውን ከእንክርዳዱ ሳይለይ ሰብስቦ
በግዴለሽነት አቀረበ። ወኢነጸረ እግዚአብሔር ላዕለ ቃኤል ወላዕለ
መሥዋዕቱ ይላል፤ የልቡን ጠማምነት የመሥዋዕቱን ክፋት አይቶ
መሥዋዕቱን ሳይቀበልለት ቀረ፤ በምን ታውቋል ቢሉ ቁራ መጥቶ
በተነበት፤ በዚህ አዝኖ ተክዞ ሳለ፤ ሰይጣን መጥቶ አ አዛል ምንት
ያቈክዘከ እንዳንተ ያለ ጽኑዕ አርበኛ ምን ያሳዝንሃል? አለው።
እግዚአብሔር ቢያደላ በእኔ ላይ አዳም ቢያደላ በእኔ ላይ፤ አዳም የእኔን
መልከ መልካም ለሌላ ሰጠብኝ፤ እግዚአብሔር ደግሞ የእርሱን
መስዋዕት ተቀብሎ የእኔን መስዋዕት ሳይቀበል ቀረ እንደ እኔ ያለ ጽቁ
(ጥቁ) ወዴት አለ ብሎ እያዘነ ሲሄድ ሰይጣን በሰው ተመስሎ
የእግዚአብሔርን ነገር ተወው እሱን ገለህ ሁለቱንስ ማን ይነሣሃል
ለምን አትገለውም በዚያውስ ላይ አባትህ አዳም ከእግዚአብሔር ጋር
ተጣልቶ ተፈርዶበት የለምን ለምን ትሰማዋለህ አለው፤ ቃኤልም

[52] እግዚአብሔር ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ። ኦሪት ዘፍጥረት ፬ ፥ ፬

መግደል ምንድን ነው? አለው፤ ወራው ይወራል እንጂ ከዚያ በፊት ተደርጎ አያውቅምና፤ ቆይ ላሳይህ ብሎ አንዱ ሰይጣን በቁራ ተመስሎ አንዱ ሰይጣን በሰው ተመስሎ ስንዴውን በተነበት ደንጊያ አንሥቶ ራሱን አለው የሞተ መሰለው። ለካ ሞትም አለ? ብሏል። ከዚያ በኋላ ነዐ እጉየ ንሑር ለሐውጾተ ተክል ወንድሜ! ና ተክል ጎብኝተን እሸት በልተን ውኃ ጠጥተን አየር ተናፍሰን እንምጣ አለው። ግሩማን አራዊት ቢጣሉንሳ? አለው የአባታችን ፈጣሪ ይጠብቀናል አለው። ሄደው ተክል ጎብኝተው እሸት በልተው ውኃ ሊጠጡ ወደ ወንዝ ወረዱ። ቃኤል ታላቅ ነውና አስቀድሞ ጠጥቶ ተነሣ። አቤል ተጎንብሼ እጠጣለሁ ሲል ደንጊያ አንሥቶ ራሱን አለው ሞተ። ገሎት ሲሄድ ጌታ በደመና ሆኖ አይቴ ሀሎ አቤል እጉከ ኦ ቃኤል አለው። ዐቃቢሁ ለአቤል እኔ የአቤል ጠባቂ ነኝ? አለው። አነ ዐቃቢሁ ለምንት ቀተልኮ ጠባቂው ባትሆንስ ለምን ገደልከው? አለው። አንድም አዳም ነው አይቴ ሀሎ አቤል እጉከ ኦ ቃኤል አለው። ዐቃቢሁ ለአቤል አለው፤ ተጠራጥሮ እየፈለገ ቢሄድ በአፉ እንደተደፋ ሞቶ አገኘው። መኑ ቀተለከ አቤል ወልድየ ልጁ ማን ገደለህ? አለው ቃኤል እጉየ ቀተለኒ ቃኤል ወንድሜ ገደለኝ ብሎ በድኑ ተናግሯል፤ አንድም ከልብሱ ላይ ተፈንጥቃ የወደቀች ደም ቃኤል እጉየ ቀተለኒ ወንድሜ ቃኤል ገደለኝ ብላ መስክራበታለች። ጌታም ቃኤልን ኩን ርዑደ ወድንጉጸ[53] ብሎ ረገመው መላ ዘመኑን ወፍ በበረረ እንጨት በተሰበረ ቁጥር ሲደነግጥ ኖሯል፤ አቤል ማለት በግዕ፣ ደመና፣ የዋህ ማለት ነው የወንድሙን ክፋት እያወቀ በየዋህነት ተከትሎታልና። አንድም በኩረ ቅቱላን ማለት ነው ከእሱ አስቀድሞ የሞተ የለምና። ቃኤል ማለት ጥሪት፣ ተጋብኦ፣ መስተገብረ ምድር፣ በኩረ ቀታልያን ማለት ነው። ጥሪት አለው ልጅ ለእናት ለአባት ጥሪት ሀብት ነውና፤ ተጋብኦ አለው ሰው ሲወለድ ከአባት ዘር ከእናት ደም ነሥቶ ነውና፤ መስተገብረ ምድር አለው ጉዛም ገበሬ[54] ነውና፤ በኩረ ቀታልያን አለው ከእሱ አስቀድሞ ሌላ የገደለ የለምና።

---

[53] በምድርላይ ኩብላይና ተቀበዝባዥ ትሆናለህ። ዘፍጥረት ፬ ፥ ፲፪

[54] ጉዛም ማለት ሀብታም ባለጠጋ፣ ባለ ጓዝ ማለት ነው።

Scanned by CamScanner

ኪሩቱ ለሴት::

ለሴት የቸርነቱን ዋጋ የምታሰጨው አንቺ ነሽ:: አቤል ከሞተ በኋላ አዳምና ሔዋን ዐሥራ አራት ሱባዔ[55] በአቤል ሞት ምክንያት አዝነው ከሩካቤ ሥጋ ተከልክለው ይኖሩ ነበር:: መልአኩ መጥቶ አዳም ማዘንህ ይብቃ አቤል ወልድከ ተሳለመ ዕፀዊሃ ለገነት ልጅህ አቤል ጸደቀ፤ ገነት ገባ ገጸ እግዚአብሔር አየ አለው:: አሁን አቤል ያንጊዜ ገነት ገብቶ ለይሆን ደጋጎቹ ምን እንኳን ወደ ሲኦል ቢወርዱም መከራው እንዳላገኛቸው ለማጠየቅ ነው:: ነፍሶመሰ ለጻድቃን ውስተ እደ እግዚአብሔር ወኢለከፎመ ስቃየ እሳት እንዲል::[56] አዳምም ይህን ሰምቶ ደስ ቢለው አእመራ አዳም ለሔዋን ይላል ሔዋንን በግብር አወቃት፤ ሴት ተወለደ:: ሴት ማለት ቸር ትክ ምትክ የአቤል ፈንታ የኀዘን ማስረሻ ማለት ነው:: አክብር አባከ ወእመክ እናትና አባትህን አክብር የምትል ሕገ ኦሪት ወደ ፊት እንደምትሠራ በልቡናው ተገልጦለት እናት አባቱን ጦሮ አክብሮ አገልግሎ የቀበረ እሱ ነውና::

ወምግባረቲሁ ለሄኖክ::

የምግባር ስልቱ ብዙ ነውና ምግባራቲሁ አለ እንጂ ምግባሩ ሲል ነው:: ለሄኖክ የምግባሩን የትሩፋቱን ዋጋ የምታሰጨው አንቺ ነሽ:: ወእምቅድመዝ ነገር ተከብተ ሄኖክ ወአልቦ ዘአእመረ በጎበ ተከብተ ይላል ሄኖክ እግዚአብሔርን ማገልገል ከሴት ርቆ ንጽሕናን ጠብቆ ከዓለም ተለይቶ ከምግብ ተከልክሎ ነው እንጂ ብሎ በዚህ ዓለም ሦስት መቶ ስድሳ አምስት ዘመን ኖሮ ይህ ዓለም ካልተዉት አይተውም ካልጠገቡት አይጠገብም ብሎ ቤቱን ንብረቱን ለልጁ ለማቱሳላ አውርሶ ሄዶ በእግረ ገነት ወደቀ:: በእገረ ገነት ሰባት ዓመት ኖሯል:: ምነው አሁን ወአልቦ ዘአእመረ በጎበ ተከብተ ብለን አልነበረም ቢሉ? ከዚያው በምሥራቅ ይሁን በምዕራብ፤ በሰሜን ይሁን በደቡብ አልታወቀምና:: ሄኖክ በምግባር በሃይማኖት በትሩፋት እግዚአበሔርን ደስ ቢያሰኘው ከረዐይት ከፍዳቸው ከግብራቸው ጠብቆ ከዐይነ ሞት ሰውሮታል:: ሄኖክ ማለት ተሐደሰ ማለት ነው:: ይህስ ቀድሞ ብሌት ነበረበት ያሰኛል ብሎ ሐዲስ ማለት ነው:: አዳም ዕፀ በለስን በልቶ ብሌትን (እርጅናን)

---

55 አንዱ ሱባዔ ሰባት ዓመት ነው፤ ሰባቱ ሱባዔ አንድ ኢዮቤልዩ ነው፤ አንድ ኢዮቤልዩ አርባ ዘጠኝ ዓመት ነው፤ ሁለት ኢዮቤልዩ ሄኖ ዓመት ነው:: ዘሌዋውያን ፳፭ ፥ ፰

56 የደጋግ ሰዎች ነፍስ ግን በእግዚአብሔር እጅ ናት የኃጢአተኞች መከራ አላገኛቸውም:: ጥበብ ፫ ፥ ፩

እንዳመጣ ሄኖክ ግን ከምግብ ተከልክሎ መታደስን አምጥቷልና። ከአቤል መሥዋዕት የሄኖክ መሥዋዕት ይበልጣል። አቤል መሥዋዕት ቢሠዋ ምን ተጠቀመ አላለምና። አንድም ሞት እንዳለ በአቤል፤ ትንሣኤ እንዳለ በሄኖክ ታውቋል። በአቤል አፍርሆ፡ ወበሄኖክ አንቅሖ፡ እንዲል።[57]

ታቦት እንተ ኖኅ በዘባቲ ድኅነ እምአኩይ አይኅ።

ኖኅ ከማየ ሥራዊ ከማየ ድምሳሴ የዳነብሽ መርከብ አንቺ ነሽ። በኖኅ ዘመን የነበሩ ሰብአ ትካት እንደ ፈረስ ጆሮ እንደ ጠር ጉሮሮ ተስተካክለው ለፈጣሪያቸው ያልተመቹ ኀጢአትን ቢሠሩ የማይሰለቹ ሰውነታቸውን እንደ ግብር አባታቸው እንደ ዲያብሎስ ያረከሱ በአስተሳሰብ ከእንስሳት ያነሱ በክፋት ከሚባሉ አራዊት የባሱ ነበሩ። ከክፋታቸውም እንዲመለሱ እግዚአብሔር ወራትን አስፍቶ ዘመናትን አበዝቶ ቢሰጣቸውም የማይመለሱ ሆኑ፤ ጌታ ለኖኅ ማየ አይኅ የማዘንም ነኝና መርከብ ሥራ ብሎታል። በምን ያህል ዘመን ታዘንማለህ? አለው። በመቶ ኻያ ዘመን አለው። አያይዞም እንዴት እንደሚሠራም ይነግረዋል፤ ሞላልነቱን ሦስት መቶ፤ ወርዱን ሃምሳ ክንድ፣ ቁመቱን ሠላሳ ክንድ አድርገው፤ ዐሥር ክንድ ሠርተህ ደርብ፤ ዐሥር ክንድ ሠርተህ ደርብ ሥራለት። ወዘአሐቲ ተርፈተከ አንዲት ስትቀርህ መስኮት አውጣለት። ሦስት ሦስት ዕርከን አብጅለት፤ በብረት እያያዝክ በኖራ እየለበጥክ ሥራ ብሎታል። ወዲያው ወዐቀመ ዕፀዊሃ ለገነት ይላል ፈጥኖ የሚያድገውን እንጨት እየተከለ በመላእክት አጋዥነት ይሠራ ጀመር። ሲሠራ ሰብአ ትካት መጥተው ኖኅ ምን ትሠራለህ? አሉት። ጌታ ማየ አይኅ የማዘንም ነኝና መርከብ ሥራ ብሎኝ እሠራለሁ አላቸው። በምን ያህል ዘመን አዘንማለሁ አለህ? አሉት። በመቶ ኻያ ዘመን አላቸው። በል አንተ ጥቂት ነህ በዚያውም ላይ አርጅተሃል ሥራ፤ እኛ ግን መቶውን ዘመን ተጫውተን ስቀን ተደስተን የወደድነውን ፈጽመን በኻያው ዘመን እንሠራለን ብለው እየዘበቱበት ሄዱ። እግዚአብሔር የማይሠራውን አይናገር የተናገረውን አያስቀር ብሎ መላእክት ከገነት ቀሊላን ዕፀዋት እያመጡለት ዕለቱን ሥራ ጀምሯል፤ በሁለት ጐልቋ ኢዮቤልዩ ሦስት ክፍል አድርጎ ሠርቶ

[57] ሄይማኖተ አበው ዘኤጲፋንዮስ ፶፱ ፥ ፩

ጨርሷል። ኖኅም ሠርቶ ሲጨርስ ጌታን ምን ላድርግ? አሰው። ጌታም ከሚበሉ ሰባት ሰባት፤ አምስቱ ለምግብ ሁለቱ ለዘር፤ ከማይበሉ ሁሉት ሁለት ለዘር ብቻ ሴትና ወንድ ይዘህ ግባ በሎታል። እንደምን ሆነው ይሰበሰቡልኛል? አለው። መጥቅዕ ምታ ይሰበሰቡልሃል አለው፤ መጥቅዕ ቢመታ በተአምራት ተሰብስበውለታል። አንድም መልአኩ በኅፉስ አውታር ሰብስቦለታል። ሦስቱን ልጆቹን ከሚስቶቻቸው እሱ ከኅሚስቱ ስምንት ራሱን ሆኖ ገብቷል። ሴቶች ልጆቹን በግራ ወንዶች ልጆቹን በቀኝ እሱ በመካከል ዐጽመ አበውን እንደ ታቦት አድርጎ ወደ መርከቢ ገባ። ስለምን ቢሉ ተላልፈው ኀጢአት እንዳይሠሩ ነው። ከዚህ በኋላ ግጠማት አለው ገጥሟታል። ራስ ሲመለጥ ዘመን ሲነጉድ አይታወቅምና መቶ ኻያ ዘመን ተፈጽሞ አርባ መዓልት አርባ ሌሊት ዘንሚል። ከላይ በሰባት ከታች በሰባ አፍ ፈልቷል፤ የላዩ የሚልጥ የታቹ የሚያገለባብጥ ነው፤ ከግንቦት መድኃኔ ዓለም ጀምሮ እስከ መስከረም ኻያ ሰባት ድረስ እየጐደለ ሄዷል። መርከቢቱን መልአኩ ወስዶ ከአራራት ላይ አኑሯታል፤ ከዚህ በኋላ መርከቢ እየተንሳፈፈች ከምድር ዐሥራ አምስት ክንድ ያህል ወጥታለች። አራራተ ነበረት ታቦት ያሰኘው ይህ ነው። ይህ ምሳሌ ነው፤ መርከብ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ፣ ሦስት ክፍል መሆንዋ ቤተ ክርስቲያንም ሦስት ክፍል ናትና ማኅሌት፣ ቅድስት፣ መቅደስ፤ አንድም የሥላሴ ማደሪያ ናትና፤ በውስጥ የዳኑ የምእመናን፣ በውጭ ያለቁት የአረማውያን ምሳሌ። አንድም መርከብ የሥልጣነ እግዚአብሔር፤ በአፍአ ያለቁ የኀጥአነ ብሊት፣ በውስጥ የዳኑ የጻድቃነ ብሊት ምሳሌ፤ ነፍሶሙሰ ለጻድቃን ውስተ እደ እግዚአብሔር ወኢለከፎሙ ስቃየ እሳት እንዲል ወደ ሲኦል ምንም ቢወርዱ ደጋጉን መከራው አላገኛቸውምና። አንድም መርከብ የእመቤታችን ምሳሌ ከመርከብ ድነው የወጡ ፍጥረታት ዓለም እንደሞሏት በድንግል ማርያም ምክንያት ከሲኦል የወጡ ነፍሳት ገነትን ሞልተዋታልና፤ ኦ እግዝእትየ ማርያም ለተረፈ ዓለም ማሕየዊት ዕፀ። አዕፀቀ ፍጥረት ሐዲስ እንተ እምኔሃ ሠረፀ እንዲል።[58] አንድም መርከብ አይለወጥም የእመቤታችን ያቺ ሦስት ክፍል እንደሆነች እመቤታችን የሥላሴ ማደሪያ ናትና። አንድም ሦስት ዕርከን አብጀለት

[58] እመቤቱ ማርያም ሆይ የሐዲስ ፍጥረት ቅርንጫፎች ከእርሷ የበቀሉ ከዓለም የተረፉ የኖኅ መዳኛ መርከቡ አንቺ ነሽ። እንዚራ ስብሐት

አለው ጌታ ከእመቤታችን ሳይወለድ የሥላሴ አንድነታቸው ሦስትነታቸው ተለይቶ አልታወቀምና፤ መኑሂ እምኢያእመሮመ ለሥሉስ ቅዱስ ዘእንበለ እምድኅረ ተሠገወ ወልድ ዋሕድ እምቅድስት እመ እንዲል። አንድም የንጽሐ ሥጋ የንጽሐ ነፍስ የንጽሐ ልቡናዋ ምሳሌ። አንድም በሦስት ዓለማት ትመሰገናለችና በዚህ ዓለም፣ በገነት፣ በመንግሥተ ሰማያት ትመሰገናለችና አንድም በነገደ ሴም፣ በነገደ ካም፣ በነገደ ያፌት ትመሰገናለችና። አንድም በወጣንያን፣ በማዕከላውያን፤ በፍጹማን አንደበት ትመሰገናለችና። አንድም በመላእክት፣ በደቂቀ አዳም፣ በካልዕ ፍጥረት ትመሰገናለችና። በአፍአ ያለቁ በእመቤታችን ቃል ኪዳን የማያምኑ የአረማውያን የመናፍቃን፣ በውስጥ የዳኑ በእመቤታችን ቃል ኪዳን የሚታመኑ በተስፋዋ የሚማፀኑ የምእመናን። አንድም መርከብ የመስቀል ምሳሌ ሦስት መሆኑ የፈያታይ ዘየማን የፈያታይ ዘጸጋም መካከሉ የጌታ ምሳሌ። አንድም የጌታ ብቻ ሦስት ይሆናል ግራ እጁ፣ ቀኝ እጁ፣ መካከል ሰውነቱ በአፍአ ያለቁ በመስቀል ያላመኑ በውስጥ የዳኑ በመስቀል ያመኑ ምእመናን ምሳሌ። አንድም መርከብ የትንሣኤ ምሳሌ ሦስት መሆኑ ጌታ ሦስት መዐልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ የመነሣቱ፤ በአፍአ ያለቁ በትንሣኤ ያላመኑ በውስጥ የዳኑ በትንሣኤ ያመኑ ምእመናን ምሳሌ። አንድም መርከብ የጥምቀት ምሳሌ ሦስት መሆኑ የሚጠመቁት በሦስቱ ስም ነውና በስመ አብ፣ በስመ ወልድ፣ በስመ መንፈስ ቅዱስ፤ በአፍአ ያለቁ በጥምቀት ያላመኑ በውስጥ የዳኑ በጥምቀት ያመኑ ምእመናን ምሳሌ። ከሦስት መቶ ሠላሳው ዐሥራ ሁለት ቢነሡለት ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት ይሆናል የሦስት መቶ ዐሥራ ስምንቱ ሊቃውንት ምሳሌ፤ ዐሥራ ሁለቱ የዐሥራ ሁቱ ሐዋርያት ምሳሌ፤ ወርዱ ሃምሳ መሆኑ የሃምሳው ሊቃውንት ምሳሌ። በመግቢያው ላይ ያሉት የሰማዕታተ ብሌት ምሳሌ መከራ ይጸናባቸዋልና፤ በከበሮ ቤት ያሉት የሰማዕታተ ሐዲስ መከራ ነፍስ የለባቸውምና፤ በብረት እያያዝክ በኖራ እየለበጥክ ሥራ አለው፤ የፍቅረ እግዚአብሔር የፍቅረ ቢጽ ምሳሌ። የእነዚህ ሁሉ ምግባቸው አንድ ሥጋ ነው። ምእመናንም በግእዝ ርትዕት አንድ ናቸውና። ኖኅ ማለት ጉልቁ ትሩፍ፣ ትፍሥሕት ዕረፍት ማለት ነው። ፍጥረታት እንዲተርፉ ምክንያት ሆኗልና።

Scanned by CamScanner

ለሴም የመባረኩን ዋጋ የምታሰጪው አንቺ ነሽ፤ አንድም የሴም ምርቃቱ በረከቱ አንቺ ነሽ። ኖኅ ከመርከብ ከወጣ በኋላ ገበሬ ሆነ ወይን ተከለ፤ ከወይን ጠጁም ጠጥቶ ሰከረ፤ ዕራቁቱን ሆኖ ሳለ ከነአን የተባለው የልጅ ልጁ የአያቱን ዕርቃን አይቶ ሄዶ ለአባቱ ለካም ነገረው። ካምም የአባቱን ዕርቃን አይቶ እየሳቀ እየተሳለቀ ለሁለቱ ወንድሞቹ ሄዶ ነገራቸው፤ ሴምና ያፌት ግን የአባታችንን ዕርቃን አናይም አናሳይም ብለው የኋሊት ሄደው ልብሳቸውን አልብሰውታል። ይህ ምሳሌ ነው፤ ኖኅ የጌታ፣ ወይን የፍቅር፤ ኖኅ ሰክሮ ዕርቃኑን እንደሆነ ጌታም በሰው ልጅ ፍቅር ሰክሮ ዕራቁቱን የመሰቀሉ ምሳሌ፤ ፍቅር ሰሐቦ ለወልድ ኀያል እመንበሩ ወአብጽሖ እስከ ለሞት ብሎ ወደ ፊት እንዲያመጣው። ከነአን የይሁዳ ከነአን የኖኅን ስካር አይቶ ለካም እንደተናገረ ይሁዳም ደቀ መዝሙር መስሎ ቀርቦ ጌታን በመሳም አሳልፎ ለጸሐፍት ፈሪሳውያን የመስጠቱ ምሳሌ፤ ካም የጸሐፍት ፈሪሳውያን ምሳሌ ካም በአባቱ ዕርቃን እንደተሳለቀ ጸሐፍት ፈሪሳውያንም በጌታ ዕርቃን የመዘባበታቸው ምሳሌ፤ ሴምና ያፌት የፀሐይና የጨረቃ ምሳሌ፤ ሴምና ያፌት የአባታችንን ዕርቃን አናሳይም ብለው ልብሳቸውን የኋሊት ሄደው እንዳለበሱት ፀሐይና ጨረቃም የጌታችንን ዕርቃን አናሳይም ብለው ብርሃናቸውን የመንሣታቸው ምሳሌ፤ ወጽሐወ ኖኅ እምስካረ ወይኑ እንዲል ምንም ቢሆን ስካር ፈጽሞ አእምሮ አይነሣምና ታናሽ ልጁ ካም እንደተዘባበተበት ባወቀ ጊዜ ከነአን ይኩን ገብረ ለአኃዊሁ ከነአን ለወንድሞቹ ባርያ ይሁን ብሎ ረገመው፤ ያፌትን ለያርብሕ ደወሎ ለያፌት እግዚአብሔር የያፌትን ግዛት ያስፋ ብሎ መረቀው፤ ሴምን ለይኅድር እግዚአብሔር ውስተ ጽርሑ ለሴም ብሎ ባረከው፤ የሴም ድንኳን የተባለች ስጊዜው ሐይመተ አብርሃም ስትሆን ፍጻሜው ግን አማናዊት ድንኳን እመቤታችን ናት፤ ኖኅ ምስለ ወልዱ ይዌድስኪ እስመ በላዕሌኪ ተፈጸመ ቃለ በረከቱ ዘይቤ ለይኅድር እግዚአብሔር ውስተ ቤቱ ለሴም እንዳለ ደራሲ።።[59]

---

[59] ኖኅ ከልጁ ጋራ ያመሰግንሻል በሴም ድንኳን እግዚአብሔር ይደር ብሎ የተናገረው የበረከቱ ቃል በአንቺ ተፈጽሞዋልና። አርጋኖን ዘሰኑይ

ወክፍል ሎቱ።

የሴም እድል ፈንታው ጽዋ ተርታው አንቺ ነሽ። ኖኅ ከመርከብ ከወጣ በኋላ መሥዋዕት ሠዋ፤ ጌታ ኖኅን ዳኛ መልአኩን ሽማግሌ አደርጎ የሦስቱን ልጆቹን ስም በቅፋፍ ጽፎ ይህን ዓለም በዕጣ አካፍሏቸዋል። ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ቀኝ ቀኙን ለያፌት፤ ግራ ግራውን ለካም መካከሉን ለሴም አካፍሏቸዋል። እመቤታችን ተወልዳ ያደገችበት ልጇ ክርስቶስ የተወለደባት ተአምራት የተደረገባት ደጋጉ አህጉር የእሱ ዕጣ ናቸውና፤ ወክፍል ሎቱ አለ። ሴም ማለት ሥዩም ቡሩክ ሠናይ ማለት ነው። አንቺ ውእቱ ቤተ ሴም ዘበጸሐኪዮ በዕፃዌ እምአኃዊሁ ዘበኪ ተሰልጠ በረከተ ኖኅ አቡሁ እንዳለ ደራሲ።[60]

Scanned by CamScanner